# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 31

መስከረም 8 ቀን 1015 ዓም (18-09-2-22)

በዛሬው አገር እንዴት ሰነበተች ቅንብራችን እንዳለፉት ጊዜያቶች በአገራችን የተከናወኑትንና የተከሰቱትን ሁለገብ እርዕሶች አንስተን የምንተችበት አይሆንም፣አገራችን ካለችበት ቀውስና ጦርነት ተላቃ ያዬንበት፣ካለፈው ጊዜ የተለዬ ሁኔታ ላይ የገባችበት ስላልሆነ የነበረው እዬተባባሰ በመምጣቱ ብቻ መልኩን እዬቀዬረ እንጂ ለውጥ የታዬበት ጉዳይ ስላልሆነ አድማጭን ላለማሰልቸት ስንል ጊዜና ትኩረት ልንሰጠው አልወደድንም።በነበረውና ባለው ችግርና ቀውስ ላይም አስተያዬትና የመፍትሄ ሃሳቦችን ስላቀረብን ያንን ለመደጋገም አንሻም።የዓመት ልውውጥ ቢኖርም እንደ ስርዓቱ መተካካት አዲስ ነገር ይዞት የመጣው ነገር የለም።በአጭር አባባል በአሮጌ ጠርሙስ ውስጥ የነበረውን መርዝ በአዲስ ጠርሙስ ገልብጦ እንደማቅረብ ነው።ጠርሙሱን ሰብሮ መርዙን ካልደፉት በቀር ጤና የለም። በተመሳሳይም ያለው የጎሰኞች ስርዓት ካልተወገደ በቀር ሰላምና አንድነት አይኖርም።ይህንን ወደ ተግባር የመለወጥ ሃላፊነትና ግዴታ ያለበት የችግሩ ተሸካሚ የሆነው ሕዝብ ስለሆነ የቤት ሥራውን ለእሱ ትተነዋል።

በዛሬው ቅንብራችን ለማንሳት የወደድነው ቢኖር በአንድ አንገብጋቢና ሁሉም እያነሳ በሚጮህበት "ሰላም" በሚለው ዙሪያ ላይ ነው። ሰላምን ሁሉም ያነሳል ፣ይፈልጋል።ጸረ ሰላም የሆኑትም ወያኔና ብልጽግና ተብዬዎቹ የሕዝቡን የሰላም ጥሪና ፍላጎት ጠልፈው ስለ ሰላም ያወራሉ።አባብ ለአባብ ይተያያል ካብ ለካብ እንዲሉ ሰላምን የመደበቂያ ጋሻቸው አድርገውታል።በሰላም ይቀልዱበታል። ለእነሱና ለመሰሎቻቸው ሰላም ማለት ተረጋግተው ካለማንም ተቃዋሚ አገር መዝረፍና ማፍረስ የሚችሉበት ዕድል መኖሩ ብቻ ነው።የሰፊው ሕዝብም ሆነ የእኛ ሰላም ከነሱ ሰላም የሰማይና የመሬት ያህል እርቀት አለው።የእኛ ሰላም ማለት ለእንደነሱ ላለው ጸረ ሰላም፣ ወንጀለኞችና ጨካኞች ጸር የሆነ፣ ሊቀጣ ብሎም ሊያጠፋቸው የሚችል፣ዳግም ሕዝብ ሳይረበሽ፣ ሳይፈራና ሳይከፋፈል፣ጦርነትና ግጭት የማይኖርበት፣የአገር አንድነትና ልዑላዊነት ፣የሕዝቡ መብትና እኩልነት የሚከበርበት በፍትሕ ላይ የቆመ ሥርዓት ሰፍኖ ዘላቂ ሰላም መኖር ሲችል ማለታችን ነው።

ለመሆኑ ሰላም ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን እንፈትሽና ማን ለሰላም እንደቆመ ወይም እንዳልቆመ እንድረስበት። ሰፊ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች ስለ ሰላም በዓለም አቀፍ አንዱ በሆነው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይህንን ብለዋል

"Peace means freedom from disturbance,tranquility.a state of period in which there is no war,or a war has ended."

"Peace is an important moment of rust in harmony ,in the absence of disturbance.the word peace is a state of harmony characterized by the lack of violence,conflict behaviors and the freedom from fear of violence."

"commonly understood as the absence of hostility,peace also suggests the existence of healthy or newely healed interpersonal or international relationship,prosperity,in

matters of social or economic welfare,the estabilishment of equality and a working political order that serves the true interests of all"

"Peace reduces stress or anxiety and allows one to be free from worry,peace is a fruit of spirit

የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን እንስሳት፣ አእዋፍም ሆኑ አራዊቶች ሰላም ይፈልጋሉ፤ሁሉም ሳይረበሹና ሳይጨነቁ የሚገፉትን የተፈጥሮ ኑሮ መኖር ይሻሉ።አንዱ በሌላው መጠቃትን አይወድም።ሰላም ከሌለው የሰው ልጅ ሠርቶ ማደር፣የሚፈልገውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቱን አግኝቶ፣ወልዶና ተዋልዶ ተባዝቶ መኖር አይችልም።አእዋፍ ሳይቀሩ እንቁላላቸውን ጥለው ጫጩት ሊፈለፍሉ የሚችሉት ጸጥ ባለ ቦታና ወከባ በሌለበት ውስጥ ሆነው የሚተናኮላቸውና እንቁላላቸውን ወይም ጫጩታቸውን ከስራቸው መንጥቆ የሚበላ ጠላት ካልመጣባቸውና ከስጋት ነጻ ሲሆኑ ነው።እንዲያም ሆኖ ግን ሳያስቡት ጭልፊት ቢመጣባቸው ለመከላከል በክንፍና በሹል አፋቸው ይከላለላሉ እንጂ እሽ ብለው ገብረው አይቀመጡም።ሌላውም ሁሉ እንዲሁ።

ስለ ሰላም ብዙ ጥናቶች ተካሂደዋል፣የሁሉም ጥናቶች መቋጫ የሆነው ግን አንድና አንድ ብቻ ነው።

ያም ሰላም ማለት በጣም ጠቃሚ የህይወት ጊዜ ማለትም ፍርሃትና ጭንቀት፣እረብሻና ግርግር፣አመጽና ስጋት፣ጦርነትና ግጭት የሌለበት፣ ጸጥታ፣ፍቅርና መስማማት እንዲሁም መተሳሰብና፣እርካታ ያለበት ወቅትና ቦታ ነው።በተጨማሪም አንዱ በራሱ ውስጥ ሰላማዊ ስሜት ሲኖረውና ከሌላውም ጋር በሰላም የመኖር ፍላጎትን ሲከተል በጠላትነት መፈራረጅ ተወግዶ ለጋራ ጥቅም ሲሰለፉ ያን ጊዜ ሰላም ወረደ ይባላል።

በህብረተሰብ መካከል የኤኮኖሚና የፍትሕ እኩልነት የሚያመጣ የፖለቲካ ስርዓት ሲሰፍን ሰላም ይሰፍናል።ሰላም መጨነቅና መጠበብን ያሶግዳል።ሰላም የአይምሮ እርጋታና ማስተዋልን ፈጥሮ የሰው ልጆች በፍቅር እንዲኖሩ ያበቃቸዋል።ሰላም ለምርምርና ለአዲስ ግኝት ይረዳል።በችግር ውስጥ ያልተመረዘና ያልተነከረ አይምሮ ተዝናንቶ አዲስ ነገር ለመፍጠር ጊዜና ዕድል እንዲኖረው ያደርጋል። በሰላም ውስጥ መኖር ከተቻለ ለጦርነት ለግርግርና፣ለመተላለቅ አይሰለፉም፣የጦር መሣሪያ የታሪክ ዕቃ ይሆናል፣ይቃጠላል፣ሰላም የሰፈነባት ዓለም የሰው ልጅም ሆነ ሌላው ፍጡር በሕይወት ዘመኑ ኖሮ በዕድሜው ሲያልፍ የሚቀበርባት የጋራ ቤቱ ትሆናለች።ሰላም የመንፈስ ፍሬ ሲሆን እድገትና መሻሻል፣ ደስታና እርካታ ደግሞ የሰላም ፍሬ ነው።

ሰላም ሁለት መልክ እንዳለው ተመራማሪዎቹ ይገልጻሉ።አሉታዊ፣(አፍራሽ) ሰላም (Negative peace)፣ አዎንታዊ፣(ገንቢ) ሰላም(Positive peace)

አሉታዊ(አፍራሽ) ሰላም ማለት ለጊዜው ሰላም የሰፈነ ቢመስልም ከጊዜ በኋላ የሚደፈርስ፣ለዘለቄታው ያልተቋጨ ጦርነትን የሚወልድ፣የህብረተሰቡን ልብ ያልገዛና ያላሳመነ ሰላም ማለት ሲሆን በአዎንታዊ ሰላም የተመደበው ደግሞ የመጨረሻ መፍትሔ ተሰጥቶት፣የጦርነትና ግጭት ምክንያቱ እስከነአካቴው ተወግዶ ጦርነትና ግጭት ዳግም የማይነሳበትና ዘለቄታዊ ሰላም የሰፈረበት ህብረተሰቡ የተቀበለውና የሚንከባከበው ነው ይላሉ። በተጨማሪም መዋቅራዊ የሆነ በደልና ኢፍትሃዊነት ያልሰፈነበት ሥርዓት መኖር ነው ይላሉ።ያንንም በዚህ መልኩ በራሳቸው ቋንቋ ያስቀምጡታል።

"Negative peace is defined by the absence of war and violence that does not capture a sociiety's tendencies towards stability and harmony.

“Positive Peace  an absence of Structural Violence or social justies,measures of inclusiveness,wellbeing and happiness creating an optimal environment for human potencial to florish conceptually and empirically linkd to socio economic resilience.It is also associated with better economic outcomes,measures of wellbeing,levels of gender equality and environmental performance.Peace is a relationship of the living well together.It is strong and lasting based on respect,serenity,cordiality and mutual understanding among people.”

አዎንታዊ ሰላም የህብረተሰብን መከራ የመቋቋም ችሎታንና ወደ ጦርነት ተንደርድሮ ያለመግባትን ችሎታና ብቃት መለኪያ ይሆናል።አዎንታዊ ሰላም የግጭትና ያለመተማመንን ባህል ይቃወማል፤ ያሶግዳልም።

ስለሰላም ምንነት የተሰጡትን ማብራሪያዎች ተከትለን በአገራችን ውስጥ ስላለው ሁኔታ ሰላም መስፈኑንና አለመስፈኑን፣እንዴትስ ሊሰፍን እንደሚችል ስንመረምር ይህንን ይመስላል። ሕዝብ አንዱ በሌላው ላይ እምነት አጥቶ፣በጥላቻ እርስ በርሱ እንዲባላ የሚያደርግ ሥርዓት የሰፈነበት፣ያንንም የሚያራምድ መዋቅር የተዘረጋበት ፣በጦርነትና በግጭት አውድ ውስጥ የሚናጥ ሕዝብ የሚኖርበት አገር በመሆኑም  እንኳንስ አዎንታዊ ሰላም ይቅርና ጊዜያዊ የሆነ አሉታዊ ሰላምም እንዳልሰፈነ እንገነዘባለን።ለዚህ ደግሞ ተጠያቂዎቹ የቀድሞዎቹን ትተን(እረስተን ማለታችን አይደለም) ላለፉት 32 ዓመታት ሥልጣኑን እዬተቀባበሉ የያዙት የወያኔ መራሹ የኢሕአዴግ አንድና ሁለት ጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች መሆናቸው የተረጋገጠ ነው።

እነዚህ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽ የሆኑ ቡድኖች ቀደም ሲል በኢሕአዴግነት ከአራት ዓመት ወዲህ ደግሞ በብልጽግናነት ሥልጣን የጨበጡና የነሱ መሰል የሆኑ ተለጣፊና ለሥልጣን ቅርምት የተሰለፉ የጎሳ ስብስቦች ናቸው።በመካከላቸው ሰላም እያሉ የሚጮሁትም ከላይ እንዳሳዬነው እነሱ ተስማምተው ለሚዘርፉበት ውል እንጂ ለሕዝቡ መሠረት ያለው ከጦርነትና ከግጭት፣ከዘረፋና ከድህነት ለዘለቄታው የሚገላግል ሰላም እንዲመጣ አስበው አይደለም።  “የማይተማመን ባልንጀራ በዬወንዙ ይማማላል”፤እንደሚሉት እነዚህ ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑ ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ኢትዮጵያዊነት ሃይሎች በተደጋጋሚ ስለሰላም ቢያወሩ፣ ቢታረቁ ቢፈራረሙ ለአዎንታዊ ሰላም አያበቁም።ለነገሩማ በሥልጣን ላይ ያለው አንዱ ጸረ ሰላም ብልጽግና፣ የሰላም ሚኒስትር የሚል ተቋም በሚንስትር ደረጃ አቋቁሜአለሁ ብሎ ነበር፤ግን በአገሪቱ ሙሉ ለሙሉ ሰላም ማስፈን ቀርቶ በየከባቢው ከጎሰኛ ወሮበሎች የንፁሃንን እልቂት ሊታደግና ነዋሪው የሰላም እንቅልፍ እንኳንእንዲያገኝ አልረዳውም።ይባስ ብሎ ለወንጀለኞቹ የሞራልና ድርጅታዊ ድጋፍ፣የስንቅ፣የትጥቅና የመረጃ  ተፋሰስ የሚያደርገው ይኸው በሥልጣን ላይ የተቀመጠ ቡድን ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትንሹም ትልቁም ሰላም ይመኛል፣ሰላም ይፈልጋል፣ጸሃፊው በስነጽሑፉ፣ዘፋኙ በሙዚቃው፣ደራሲው በድርሰቱ፣ሃይማኖተኛው በጸሎትና በመዝሙሩ፣ወታደሩ ሳይቀር ከጦርነት አርፎ የሚኖርበትን የሰላም ጊዜ ይናፍቃል።ሁሉም ሰላም ይላል።ሳር ቅጠሉ ሳይቀር ሰላምን ይመኛል።ይህንን ለእውነተኛ ሰላም የሚደረግ ጥሪ ጠልፈው የውሸት ሰላም ለማስፈን የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መራሹ መንግሥትና የወያኔ ቡድኖች ካገር አገር እዬዞሩ፤ አንድ ጊዜ ኬንያ ሌላ ጊዜ ጅቡቲ እዬተሽከረከሩ በአለቆቻቸው በምዕራቡ ብብት ሥር ለመፈራረም እላይ እታች እያሉ ነው።የነሱ ሰላም የሕዝቡ ሰላም አይደለም።ሕዝቡን ሰላም ያሳጡት እነሱ ስለሆኑ በሰላም ስም ዕድሜያቸውን ለማርዘም የሚያደርጉት ስምምነት ከመሆን አያልፍም።የነሱ ሰላም የውሸት ወይም አሉታዊ(Negative peace) ሰላም ነው። ለእውነተኛና ዘላቂ ሰላም(Positive Peace) የሰላም ጸር የሆኑት ሃይሎች  በጥፋታቸው ሲጠዬቁ፣

መጠዬቅም ብቻ ሳይሆን መወገድ አለባቸው።የነሱም መወገድ ብቻ ሳይሆን የበተኑት መርዘኛ የጎሳ አስተሳሰብ ከዘረጉት አገራዊ አወቃቀርና የሚመሩበት ሕገ ጥፋት ጭምር መወገድ ይኖርበታል።

ስለሰላም ምንነትን ጥቅሞች የተለያዩ አገሮች ማህበረሰቦች በዬቋንቋቸው ገልጸውታል፣ለምሳሌም ያህል

ሕንዶች ፣ ሻንቲ(Shanti) ሲሉ በመከራም ውስጥ ቢሆን የሰው ልጅ የመንፈስ መረጋጋትን የሚሰጥ ይሉታል።

ጃፓኖችም-፣ ሄይዋ(Heiwa)በማለት አንዱ ከሌላው ጋር በመጣመር ለጋራ ጥቅም መቆም ነው ይሉታል።

አይሁዶች-፣ ሻሎም(Shalom)ትክክለኛ ግንኙነት፣አንድነትና ብልጽግና የሚገኝበት ፣ከፍትህ የፈለቀ የብዙሃንነት ስሜት መኖር ሲሉ ይተረጉሙታል።

ደቡብ አፍሪካውያን ዙሉ፣- ኡቡንታ(Ubunta)ከሰብአዊነት ጋር የተቆራኘ በራስ መተማመንና ፣አንዱ የሌላው ብዙሃን መሆን እንደሆነ ገልጸውታል።

ኢትዮጵያውያን፣- ሰላም(Selam)በመቻቻልና በመተሳሰብ፣ሌላውን እንደ እራስ በማዬት፣አንዱ በሌላው ላይ ችግር ሳይፈጥር፣እራስ ወዳድነት ከሚያመጣው ተንኮልና ግጭት እርቆ በፍቅርና በእኩልነት መኖር ብለን ሰላምን በአጭሩ እንተረጉመዋለን።

ጸረ ሰላም ሃይሎች ካልጠፉ ሰላም እንደማይሰፍን እናውቃለን።ያንንም በተግባር ለመግለጽ ጸረ-ሰላም የሆኑትን ሃይሎች እንታገላለን።የውጭ ሃይሎችና ለነሱም መግቢያ ቀዳዳ የከፈቱትን ወያኔንና ብልጽግናን እንዲሁም ሌሎቹን በዬጎሳው ስም ታጥቀውና ተደራጅተው ሰላም የሚነሱትን ጸረ ሕዝብ፣ ጸረ አገር፣ጸረ አንድነት፣ጸረ እድገት የሆኑትን ሁሉ እንታገላለን።ከጎሰኝነትና ከነጠላነት ይልቅ በኢትዮጵያዊነትና በብዙሃንነት በሰላም ለመኖር እንታገላለን።ለዚያም የሚከተለው ሙዚቃ በኪነት ባለሙያዎቻችን የቀረበ ማስረጃችን ነው። ሰላም ለአገራችን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም እንዲሆን፣ ለሰው ልጆች ብቻም ሳይሆን ለእንስሳትና ለአዋፋት ጭምር እንዲሆን በድምጻዊው መሀሙድ አህመድ ባቀነቀነው የሙዚቃ መልእክታችን እንዲህ ገልጸናል።

https://yuotu.be/E2Vun-4DqfA

ለማጠቃለል

ከላይ የተተነተነው የሰላም ትርጉምና ጥቅም ባብዛኛው መልኩ በአንድ አገር ሕዝብ መካከል የሚኖረውን አለመግባባትና የሰላም መደፍረስ የሚመለከት ሲሆን በአጠቃላይ በሰው ዘር መካከልም ሊኖር የሚገባውን ሰላም ለማሳዬት ተሞክሯል።ይህ በሰዎች መካከል ሊሰፍን የሚፈለገው ሰላም አንጻራዊ እንጂ የሰው ልጆችም ሆኑ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት ሁሉ ከሁሉም አይነት መከራ የሚላቀቁበት ዘለቄታዊ ሰላም ይኖራል ማለት አይደለም።ከጦርነትና ከእርስ በርስ ግጭት ቢላቀቁም ከጠፈጥሮ ጋር የሚደረገው ግብግብ ይቀጥላል።የተፈጥሮ ውጣ ውረድ፣መዛባትና የሚያስከትለው የለውጥ ሂደት በራሱ የሰላም ኑሮን ያናጋል።እርሃብ ቢከሰት፣ጎርፍ ቢያጥለቀልቅ፣መሬት ቢንቀጠቀጥ፣ማዕበል ቢነሳ፣መሬት ቢደረመስ፣አዬርና ውሃ ቢበከል---ወዘተ ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር አይቻልም።ሁሉም ነገር ይናጋል።ያንን አደጋ ለመቋቋም በሚያስችለው መንገድ ሁሉ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፤እርፎ መቀመጥ የለም። ለዚያ ግን ሕዝብ በራሱ መካከል የሚኖረውን የእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት ማሶገድ አለበት።ካልሆነ

ለሚገጥመው የተፈጥሮ ወለድ ችግሩ መፍትሔ ለመፍጠር ዕድልና ብቃት አይኖረውም።ኑሮው ሰላመቢስ፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሆንበታል።

ሌላው ደግሞ የአንድ አገር ሕዝብ በሰላም ቢኖር እንኳን፣ የውጭ ወራሪዎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ በሰበብ ባስባቡ ገብተው ሰላሙን እንደሚነሱት ታውቆ በዚያም በኩል በቂ ዝግጅት መኖር አለበት። ከሚገቡበትም ቀላሉ መንገድ ነዋሪውን ሕዝብ በመከፋፈል በማንነቱና በሚከተለው እምነት ከለላ ሰርገው መግባት ስለሆነ በዚያም በኩል ቀዳዳ እንዳይኖር በጠንካራ አገራዊ ስሜት ላይ የተገነባ አንድነት ሊኖር ይገባል።በችግርና በድህነት ብሎም በበሽታ እንዲማቅቅ ማድረጉም ሌላው በእርዳታ ስም የሚገቡበት በር ነው።ሌላው ቀርቶ የሰላም አስከባሪና ተቆርቋሪ መስለው በመግባት ብዙ ጉዳትና ስብራት እንደሚያደርሱ መታወቅ አለበት።ለአንድ አገር ሕዝብ ለሰላሙ ዋስትናው፣ ዳኛውም ሽማግሌውም እራሱ ነው።ከራስ በላይ ነፋስ እንዲሉ! አሁን ዳር ዳር እያሉ በተባበሩት መንግሥታት በተባለው የዘራፊዎችና የወራሪዎች ዋሻና ድንኳን በኩል የሚያቀነቅኑት የሰላም እንጉርጉሮ የዚያ መንደርደሪያ ነው።የአንድ አገር ሕዝብ የድረሱልኝ ጥያቄ ሳያቀርብና ሳይፈቅድ በሰላም አስከባሪ ስም ዘሎ መግባት ለይምሰልም ቢሆን በድርጅቱ ሕግ (ቻርተር) ላይ የሰፈረውን ልዑላዊነትን የሚጻረር ነው።ለሰላም የሚደረግ ጥረት ሳይሆን ሰላምን ይበልጥ የሚያናጋ ወረራ ነው።ለምዕራባውያኑ ሰላም ማለት እንደፈለጉ የአንድን አገር የተፈጥሮ ሃብት የሚመዘብሩበት ሁኔታ መፍጠር ማለት ነው።ለዚያ የሚያገለግል መንግሥት ለነሱ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ነው።ሕዝቡን ቀቅሎ ቢበላ ደንታቸው አይደለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለበት መቀመቅና ችግር ለመውጣት ትግል ለማድረግ ሲነሳ በቅድሚያ የጠላቶቹን ካምፕ ማወቅ ይኖርበታል።አንደኛውን ጠላቱን በሚናገረው ቃላት ወይም የገንዘብ ተፋሰስ ተጭበርብሮ በአጋርነት አይቶ መቀበል አደጋው ከፍተኛ ይሆናል።ሌባ አላስገባ ያለውን ሃይለኛ ቤት ጠባቂ ታማኝ ውሻ በማባበልና መርዝ የተለወሰ ሥጋ ሰጥቶ እንደሚያሶግደው ሁሉ ደሃን ሕዝብ በጊዜያዊ እርዳታ ማታለል የዚያው አይነት ብልሃት መሆኑን መገንዘብ ከጥቃት ያድናል።ባለው አነስተኛ ያገር ሃብት ተማምኖ፣በሥርዓቱ በመተዳደር ለከፍተኛ ብሔራዊ ሃብት ለመብቃት ጥረት ማድረግ ዘለቄታ ላለው ሰላምና የተከበረ አገር ባለቤትነት ያበቃል።ያንን በተግባር ሊገልጽ የሚችል አገር ወዳድ መንግሥት መኖር አለበት።ለዚያም ነው በሽግግር ሃዲድ ተጉዞ ቋሚ ሕዝባዊ መንግሥት ይመስረት የምንለው።

የሰላም ጸሮች የሆኑት ወያኔና ብልጽግና ከነአጃቢዎቻቸው ይወገዱ!

ከኅሰኝነት የጸዳ የሽግግር ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም!!

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በሰላም፣ በፍቅርና በአንድነት ይኑሩ!!!